# በኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ስም የተጋለጠው የወያኔ ሴራ በሻርለት

የወያኔን የፖለቲካ አጀንዳ ለማስፈፀም የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲን መጠቀሚያ ለማድረግ የሚውተረተሩ የወያኔ ሎሌዎችና በፍርፋሪም ሆነ ፍርፋሪ ለማግኘት በሚጠባበቁ ክብረ ቢሶች አካሄድ የተጋለጠበትንና በሻርለት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የሚያስደንቅ ሕብረትና የደርስንበት ደረጃ ትንሽ ላውጋችሁ።

በሻርለት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በአዲስ መልክ ለማዋቀር የተወሰኑ በቀጥር ሰባት የሚሆኑ ግለሰቦች፤ በኋላ እንደተገነዘብነው የወያኔን ፖለቲካ ለማራመድ በሚያስችል መንገድ የተፃፈ ጥሪ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው በማይችል መንገድ ተጠራርተው የተገናኙት። ለግንዛቤ እንዲረዳን ሁለቱ ከሌላ ስቴት ወያኔ ለስራ የላካቸው፣ አምስቱ አዚሁ ሰንበት ያሉና የመለስን ምስል በቁልፍ መያዛቸው የዞ መዞር ብቻ ሳይሆን እንደ አምላካቸው የሚያዩት ሲሆኑ፤ የሚያሳዝነው ደግሞ ከሰባቱ ስድስቱ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውና መለስ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያዘውን መድሐኒት (Prescription) እዚህ በሰለጠነው ዓለምም ሲያዝላቸው መቀበላቸው ነው። ይህ ድብቅ ስብሰባ በዚህ ላይ እንዳለ ነው ዕድሜ ለተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን ምስጋና ይግባቸውና ከመሰብሰባቸው አንድ ስዓት በፊት አምስት ኢትዮጵያውያን ተቀላቅለዋቸው አስራሁለት ሆነው መሰብሰባቸውን የተረዳነው።

እነዚሁ ግለሰቦች በመጀመሪያ ስብሰባ ወቅት ነበር አሉ ግልፅ ባለ መልኩ፤ የነባሩ ኮሚኒቲ በራሱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ፈርሷል በማለት አዲስ ኮሚኒቲ መቋቋም እንዳለበት በአፅነኦት የገለፁት አሉ። እንደው ለነገሩ የድሮውም ኮሚኒቲ ቢሆን አልሸሹም ዘወር አሉ ነው። እንደሚባለው ከሆነ ከ 12 ዓመታት በፊት የተቋቋመ ነው። የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እንኳ እንደሚያስታውሰው ላለፉት 10 ዓመታት የኮሚኒቲ ቃሉን እንኳ አልሰማም እንኳን ድርጊቱን። እነዚህ የወያኔ ተላላኪዎች ወጡ ሳይወጠወጥ እንዲሉ በሚፈጠረው ኮሚኒቲ አማካኝነት ለህዳሴ ግድብ እናዋጣለን! በሃገራችን የግንባታ ሂደት እንሳተፋለን! እያሉ የወቅቱን የወያኔን የፖለቲካ ማደናገሪያ መፈክር ይዘው ብቅ ያሉት በዚያው በመጀመሪያው ስብሰባ እንደነበር ተሰብስበን በነበረበት ጊዜ በቀረበው ሪፖርት ተገንዝበናል። መቸም ሕዝቡን ሰብስበው በግለፅ ተወያይተው ማሳመን ስለማይችሉ ኮሚኒቲውን ተገን አድርገው ለመንቀሳቀስ ያሰቡት ዘዴ ነበር እንጂ ዕውነት ኮሚኒቲውን አጠናክረው በአካባቢያችን በአንድነት ላይ የተመሰረተ የኢትዮጵያውያን መረዳጃን ለመፍጠር አንዳልነበር ከላካቸው ጌታቸው ድርጊት ካወቅን ሁለት አስርት ዓመታት አስቆጠርን መሰለኝ።

የተላኩበት የፖለቲካ አጀንዳ በግለፅና ጭምብል ባጠለቁ የወያኔ ተላላኪዎች የጋራ ስብሰባ "ግምገማ" ይመስላል ያሰቡት የድሮውን ኮሚኒቲ የማፍረስ አካሄዳቸው ትክክል አለመሆኑን ሲረዱ የናቴ መቀነት አይነት ዕርስ በርሱ የሚጋጭና የውሸት ድሪቶ የሆነ የማደናገሪያ ፅሑፍ

ለማሰራጨት የሞከሩት። በዚህ በነፃ አገር ተቀምጠው ከልባቸው ያመኑበትን ነገር መግለፅ ሲገባቸው መሳሪያ ለመሆን ራሳቸውን ማቅረባቸው ባንድ በኩል እንዴት እንዳሳዘነኝ ልነግራችሁ ባልችልም በሌላ ብኩል ደግሞ በጌታና በሎሌ ያለው ግንኙነት ለሎሌው የተላከውን የማድረስ እንጂ የማመዛዘን ስልጣን ስለማይሰጠው (አይገባኝም ብሎ ስለሚያስብ) ብዙም አልፈርድም። አንዳዶቹም ቤተ ክርስቲያን ሲመላለሱ አያለሁና አንድ ቀን እግዚአብሔር ነፃ አድርጎ የፈጠረላቸውን አእምሮ እንዲጠቀሙበት ሊረዳቸው እንደሚችል ተስፋ አለኝ። ለወደፊቱ ተስፋቸው ሊረዳቸው ይችላልና ለነሱም ቢሆን የሰሩትን ማሳየት ተገቢ ስለሚሆን ወደ ጉዳዩ ልመለስ።

ለህዳሴ ግድብ በሚል ሰበብ ለጌቶቻቸው ኪስ ማደለቢያ ኮሚኒቲውን የመለመኛ ገፀ በረከት ከማቅረብ በተጨማሪ ሌላም የተላኩበት ነገር እንዳለ "ሳይቃጠል በቅጠል" በሚል ውስጥ ውስጡን ለማሰራጨት በሞከሩት በኋላም በኢትዮሚዲያ ድረ ገፅ ላይ የወጣውንና ዲያስፖራውን በሚሳደበው ፅሑፍ ላይ የሚከተለውን እናገኛለን።

"ማንኛውም የእምነት ሥፍራ ምዕመናን ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙበት ለራሳቸውና ለሌላው ሰላምና መረጋጋት የሚለምኑበት የሚመኙበት ሆኖ ሳለ፤ መሰረቱን የሳተ የባንዲራ ምንነት ግንዛቤ በጎደለው ወይም በተሳናቸው ቡድንና ግለሰቦች ኢትዮጵያን የማይወክሉ ባንዲራዎች እየተሰቀሉ ለችግር የሚገፉፉ አትኩሮቶችን እየሳቡ ነው።" ይልና ወደ መጨረሻ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ወያኔ የሚጠቀምበትን ባንዲራ ሕጋዊነት ሲያስረዱ "የሃገሪቱ ሕዝብ በወኪሎቹ ተወስኖ በሸንጎ ያፀደቀው በሃገሪቱ ሕገ ደንብ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው የህዝቡ የመስዋዕትነት ውጤት፣ የበደሉ ካሳ፣ የትዝታው ማስታገሻ፣ የአንድነቱ መሰረት፣ የእኩልነቱ ዋልታ በመሆኑ እንደ ዓይን ብሌኑ ይጠብቀዋል እንደአስፈላጊነቱም ይከላከለዋል።"

ከዚህ አባባል እንደምንረዳው በህዳሴ ስም ኮሚኒቲውን፣ በእምነት ስም የሃይማኖት ተቋማትንና በባንዲራ ክርክር ስም የወያኔን የዘቀጠ የኋላቀር የዘውግ አገዛዝ ሥርዓትን ማስታወሻ የሆነውን ምልክት ለሀገሩ ቀርቶ ለሌው የአፍሪካ አህጉር ተምሳሌት በሆነው የነፃነትና የአንድነት ባንዲራችን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ላይ ለመለጠፍ የታለመ መሆኑን ያስገነዝበናል። በተለይ የባንዲራውን በተመለከተ ገብቷቸው ይሁን ወይም በዘውግ አስተሳሰብ ሰለባ የሆኑ አላውቅም አንድ ሁለት ግለሰቦች (የሚገርመው አሁንም ከትግራይ ተወላጆች) በ Oct. 15, 2011 ባደረግነው ስብሰባ አንስተውት በሕዝቡ ላይ የቀሰቀሰውን የቁጭት ስሜትና በአስተማማኝና በማያዳግም መንገድ የነፃነት ባንዲራችን ምን ግዜም አረንጓዴ ቢጫ ቀይ እንጂ ይህ ዘርን መሰረት አድርጎ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያሰቃየው ቡድን እላዩ ላይ የለጠፈውን "ምልክት" አለመሆኑን አስረድቷቸዋል። አንባቢው ስለባንዲራችን መረጃ በተደገፈ መንገድ ማየት ካስፈለገው ለዚህ ለወያኔ "ሳይቃጠል በቅጠል" ለሚለው መልስ የተዘጋጀውን "ሳይቃጠል ማቀጣጠል!" በኢትዮጵያ ድህረ ገጽ

http://www.ethiomedia.com/broad/sayiqatel_beqtel.pdf የተሰጠውን ትንተና መመልከቱ ከበቂም በላይ ነው። እንደው ሆደ ሰፊም ከመሆን በላይ ሆኖ ነው እንጂ የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲን እየመሰረቱ ባንዲራችንን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነገር ማንሳቱ ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ አንባቢው ሊገምተው ይችላል።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ይህ የተከራከሩበት የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለማት (ከወያኔ ምልክት ውጭ) በ 11/13/11 ላካሄዱት የዘፋኞች የሀዘን መታሰቢያ የጥሪ ወረቀት ላይ ተጠቅመውበታል። የአካሄድ አለመረጋጋትና ራዕይ በጎደላቸው ጌቶቻቸው ለብዙ ጊዜ ያየነው ተግባር ስለሆነ አሁንም በድጋሚ ሎሌ የተላከውን ማድረስ እንጂ የራሱን አቋም እንዲያንፀባርቅ ስለማይፈቀድለት ብዙም አይደንቀኝም።

ከላይ የገለፅኩት የመልዕክተኞች (የሎሌዎች) አጠቃላይ እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት በአዲስ መልክ ሁሉንም የሚያካትት ኮሚኒቲ ጋሬጣ እንደነበረ መሰረታዊ ሃሳብ ይሰጣችኋል በዬ በመገመት የነበሩ ችግሮችንና በወቅቱ የተሰጡ የመፍትሔ ሃሳቦችን ባሳለፍናቸው ሁለት ትላልቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በቀረበው ሪፖርት ባገኘሁት መረጃ መሰረት በሁለት ከፍዬ ባጭሩ ላሳያችሁ። እነዚህ ሁልት ስብሰባዎች፤ በአዲስ መልክ ለማዋቀር የተስማማንበት በ Oct. 15, 2011 ያካሄድነውና የኮሚኒቲውን አመራር በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመረጥንበት የ Dec. 18, 2011 ስብሰባ ናቸው።

### ከ Sep. 17, 2011 እስከ Oct. 15, 2011

ከመግቢያዬ ላይ እንደገለፅኩት አስራ ሁለት ሆነው በ 9/17/11 ባደረጉት ስብሰባ ላይ በሚስጥር ከተገናኙትና አሁን በዚህ ፅሑፌ ሎሌ እያልኩ በምገልፃቸው አማካኝነት ተነስቶ የነበረውን ሁሉንም ዘጋግቶ ለመሄድ የታሰበውን ፅንፈኛ ሃሳብ ተገቢ እንዳልሆነ ተማምነው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገናኝቶ የሚመክርበትንና በእንቅስቃሴ ቀርቶ በስም እንኳ ከሁለትና ሦስት ግለሰቦች በላይ የማይታወቀው ኮሚኒቲ አመራር ኮሚቴ ጨምሮ በማነጋገር ሆኔታዎች መልክ እንዲይዙ ጥረት ተደርጎ ነበር። ከሪፖርቱ እንደተረዳነው፤ በ 9/17/11 ባደረጉት የአስራሁለት ሰዎች ስብሰባ ነበር ሰባት አባለት የተመደቡበት የቀስቃሽ ኮሚቴ የተዋቀረው።

በዚህም ሂደት በኢትዮጵያውያን ከፖለቲካ ነፃ የሆነ ኮሚኒቲን የማቋቋም ፍላጎትና ድብቅ የወያኔ የፖለቲካ አጀንዳን የሚያስተናግድ ኮሚኒቲን የማቋቋም ፍላጎት አስተሳሰቦች በሚንጸባረቁበት ቀስቃሽ ኮሚቴ ውስጥ የመጀመሪያው ከ 100 ሰው በላይ የተገኘበትን የ Oct. 15, 2011 ስብሰባ እስከተጠራበት ጊዜ ድረስ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ የሆነ ውጣ ውረድ የታየበት ነበር። ከሁሉም የሚገርመው ጉዳይ ሁሉን ዘጋግተን እንጓዝ ሲሉ የነበሩት ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ግፊት እንደሚመጣ ሲገነዘቡ ጥግ እንያዝ ማለት ጀመሩ። ጥጉ ማን መሰላችሁ? በስምም ሆነ በእንቅስቃሴ የማይታወቀው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በሻርለት። ስለዚህ

እንደኪስ አውላቂ ሲያመቸው መንትፎ ለመሄድ ሳያመቸው ደግሞ ከሌላው ኪስ አውላቂ ጋር አደናግሮ እንደሚያልፈው የአንበሳ አውቶብስ ኪስ አውላቂ አንድ ላይ በመተባበር ሕዝብን መስለው ሕዝቡን ሊያፍኑት ተሯሯጡ ብዙም ተንፈራገጡ።

ይህ የቀስቃሽ ኮሚቴ የድሮውን የኮሚኒቲ ሊቀመንበር ጠርቶ ሲያነጋግር በቀስቃሽ ኮሚቴው ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚዎች ሃላፊነታቸውንና የተነጋገሩበትን በመካድ ከኘሁ የድሮ ሊቀመንበር ጋር በመወግንና የተስማሙትን በመካድ ለነባሩ ኮሚኒቲ ለማስረከብ ነው ብለው አረፉት አሉ። የ Oct. 15, 2011 ጥሪውንም ቢሆን የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለማትን ለምን ያዘ እና የመሳሰሉትን በማንሳትና ራሳቸው የተናገሩትን የኮሚኒቲውን ባዲስ መልክ የማዋቀር ሂደት ለመግታት ከፍተኛ ጥረት አደረጉ አሉ። በሃገራችን አባባል የተናገሩት ከሚጠፉ ይባላል። ለነገሩ የፖለቲካ ዘያቸው የማንነትን የማጥፋት ዘመቻ ስለሆነ ብዙ የምንደነቅ አይመስለኝም። ከከፍተኛና ዕልህ አስጨራሽ ሙግት በኋላ የተጠራው ስብሰባ እንደማይቀር ሲገነዘቡና ተላላኪዎቹ ማጣፊያው ሲያጥራቸው፤ የድሮው የኮሚኒቲው ሊቀመንበር የሰራችሁት ትክክል አይደለም ሆኖም ኢትዮጵያውያንን ማንቀሳቀስ እስከቻላችሁ ድረስ አግዛችኋለሁ ስላሉ በዚሁ ተስፋ በቀስቃሽ ኮሚቴውና በድሮው ኮሚኒቲ አመራር ነኝ ባዩ መካከል ስብሰባው እንደተጠናቀቀ ተረዳን። እዚህ ላይ የወይይቱን አንኳር ጉዳይ ብቻ አስረዳሁ እንጂ ሌላውን ተቀፅላ አልተናገርኩም። በስብሰባቸው ዕለት ከድሮው ሊቀ መንበር ጋር አብረው ከመጡት ውስጥ የአንዱን ግለሰብ ስም ስሰማ ጉድ ነው ያልኩት። ለምን መሰላችሁ? በድሮውም ኮሚኒቲ ቢሆን በሕዝብ ያልተመረጡና በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔ አምላኪም ብቻ ሳይሆኑ ወያኔ በ 2005 ቱ በተካሄደው ምርጫ የገደላቸውን ንፁሐን ዜጎች ያለመሳቀቅ ሌቦች ናቸው እያሉ ከመፈረጅ ያልተመለሱ ግለሰብ መሆናቸው በዚህ አካባቢ ስለሚታወቁ ነው። ይህን ግለሰብ ነው የድሮው የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ሊቀመንበር ነኝ ባይ ስብሰባ ይዘውት የመጡት። ለምን እንደሆነ እኔ የሚገባኝ ጉዳይ አለ። ለነገሩ የድሮው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሊቀመንበር ሲያደርጉ በቆዩበት የማህበራዊ ጉዳይ ሁሉ የወያኔ ቋሚ ጠበቃዎችን አስከትለው መሄድ ይወዳሉ። ተከታዩ ማነው አስከታዩስ ማነው የሚለው እንዳለ ሆኖ ለድሮውም ኮሚኒቲ መዳከም ለወድፊቱም ነፃው ኮሚኒቲያችንን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለማራመድ ጠንቅ ሊሆን ስለሚችል በቫርለት የምንገኝ ወገኖች እንድንረዳው፤ ሌላም አካባቢ ተመሳሳይ ጉዳይ ሊገጥማቸው የችላልና ሊያውቁት ይገባል እላለሁ።

በ Oct. 15, 2011 በተካሄደው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ሕዝቡ በማይሻማ መንገድ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በቫርለት ህልውናው እንደሌለና በአዲስ መልክ እንዲዋቀር ተወስኖ የሽግግር ኮሚቴ የተዋቀረበት ዕለት ነበር። በዚያ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የሚባልና አመራርም እንደነበረው የተረዳነው፣ አመራር ነበርን ከሚሉ ሳይቀር ኮሚኒቲው በእንቅስቃሴ ሞቶ ከተቀበረ ዘመናት ማለፋቸው የተነገረበት ወቅት ነበር። እንደወም በወቅቱ የድሮው

ኮሚኒቲ ለቀመንበር ነኝ ብለው ያየናቸው ግለሰብ፤ ኮሚኒቲውን ለመምራት "ጁሴ" አልቋል ብለው ባደባባይ መፍረሱን ያወጁበት ቀን እንደነበር ተሰብሳቢ የነበረው ሁሉ የሚያስታውሰው ነው። ስለዚህ ይህ ስብሰባ በማያዳግም መልኩ በስም እንኳን አለሁ የሚለው የድሮው ኮሚኒቲ መፍረሱ የተረጋገጠበት ነበር።

ከ Oct. 15, 2011 እስከ Dec. 18, 2011

እንግዲህ ይህን ሁሉ ሂደት ካሳለፍን በኋላና ሰባት የሽግግር አባላትን የያዘ ኮሚቴ ከተዋቀረና እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ ነው እንደገና እንሞክረው ብለው ነው መሰለኝ፤ በነሱ አመለካከት ከስህተታቸው በመማር በሚመስል መንገድ ፍቅር እንደገና ያሉት። ይሽኛው ደግሞ የህዝቡ ተወካዮች የበዙበት ኮሚቴ ስለነበርና የሕዝቡ ነፃ አስተሳሰብ ተግባራዊ እየሆነ ሲመጣ ይመስላል ምንም ሊዋጥላቸው አልቻለም። የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ በአዲስ መልክ መዋቀር አግዛለሁ ሲሉ የነበሩት የድሮው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ሊቀመንበርም ሆኑ የወያኔን ፖለቲካ ለማስረፅ በግልፅ የመጡት ተላላኪዎች በተግባር አንድ ሆነው ነበር ጨዋታ ፈረስ አካሄዳቸውን የመረጡት። ጨዋታ ፈረስ በልጅነት ሲሆን እንጂ በጎልማሳነትና በሽምግልና ሲካሄድ ራስን ከማሳነሱም በላይ በሕብረተሰቡ ዝንድም አመኔታን ስለሚያሳጣ እንኳን በግልፅ መውጣት ቀርቶ በሃሳብም ሲመጣ እንኳ ሊገታ የሚገባው ጉዳይ ነበር። መቸም አብሮ መኖር ብዙ ያሳያል። ባንድ ወቅት እኔ በምሄድበት ቤተ ክርስቲያን ሕግ እንዲሻሻል ሙከራ ሲደረግ ቦርድ ያስፈልጋል አያስፈልግም በሚል አላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ የድሮው የኮሚኒቲ ሊቀመንበር፤ በወቅቱ የነበሩትን ካህን ሕዝቡ ቦርድ እፈልጋለሁ ካለ መቀበል ግድ ነው ብለው መናገራቸውን ለተለያዩ ሰዎች ሲያካፍሉ እንደነበረ አስታውሳለሁ። ታዲያ አሁን ኮሚኒቲ መስራቹ ሕዝብ ያለው በሳቸው ዘንድ ሲደርስ አለመቀበል ትንሽም ቢሆን አያስገምታቸውም ይሆን? በሀገሬ አባባልስ ባንድ ራስ ሁለት ምላስ አያሰኝምን?

ይህ በተግባር አንድ መሆናቸው ያለምክኒያት አልተነሳም። ይህ የሽግግር ኮሚቴ ራሳቸው በተገኙበትና ባመኑበት ጭምር በተካሄደው የ Oct. 15, 2011 ከተቋቋመ በኋላ በራሳቸው አነሳሽነት ለሕዝቡ Happy Thanks giving በሚል መልዕክታቸው፤ የነባሩ ኮሚኒቲ የሚንቀሳቀስ በማስመሰል፤ ለዘመናት አስተኝተውት የከረሙትን ኮሚኒቲ፤ በሕዝቡ እንቅስቃሴ ተበረታተናል የኮሚኒቲው ስራ አስፈፃሚም በኮሚኒቲው ያገባኛል የሚሉትን ሁሉ በማማከር አስተባብሮና አፋቅሮ ኮሚኒቲውን አጠናክሮ መሄድ ይፈልጋል። አዲስ የሆኑ ኢትዮጵያውያንም ዕርዳታ ከፈለጉ ብለው የራሳቸውን ኢሜይል አድራሻ በማስቀመጥ ሪፖርት እንደሚዘጋጅና ምርጫ እንደሚካሄድ የሚገልፅ ወረቀት የበተኑት። ይገርማል። እንዴት ዓይነት መምታታት ወይም ማምታታት ነው?

በነገራችን ላይ ይህ የሽግግር ኮሚቴ ከዚህ በፊት እንደነበረው ቀስቃሽ ኮሚቴ ሁሉ የድሮውን ኮሚኒቲ ሊቀመንበር ጠርቶ እንዳነጋገረ በ Dec. 18, 2011 ለነበርነው የስብሰባ ተሳታፊዎች ተገልፆልናል። ይህን ስሰማ ኤጭ ምንድን ነው? በነፃ ሀገር የምን ልመና ነው? አልኩልኝ። በወቅቱ የተሰማኝ ስሜት እንጂ በዕውነት የኮሚቴው አካሄድ ልክ አይደለም ብዬ በማመን አልነበረም። በዕውነት እንዲህ ዓይነት ትዕግስት የተሞላበት አካሄድ በየቦታው ቢለመድ ለኢትዮጵያችን የሚያስቡ ወገኖች አንድነት ባስቸኳይ ተረጋግጦ ይህ የወያኔ ቡድን ተወግዶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተንፈስ ይል ነበር ብዬም አሰብኩ። በሽግግር ኮሚቴውና በድሮው ኮሚኒቲ ሊቀመንበር ባይ ነኝ ወደ ነበረው ንግግር ልመለስ። የንግግሩም ዋነኛ ጉዳይ Oct. 15, 2011 በተደረገውና ዕርሰዎም (ሊቀመንበሩ) ባሉበት ከዚያም አልፎ ቃልዎን በሰጡበት መሰረት የተቋቋመ የሽግግር ኮሚቴ እያለና ባዲስ መልክ የሚቋቋመውን ኮሚኒቲ ዝግጅት አንዳለ እያወቁ ለምን ሕዝቡንም ይህንንም ኮሚኒቲ ከምንም ባለመቁጠር በግለዎ በመሄድ አስፈለገዎ? የሚል ነበር። ምን አሉ መሰላችሁ አሉ፤ እንደራደር ብለው አረፉት አሉ። እንዴ፤ ድርድሩ በማን እና በማን መካከል ነው? ሕዝብ ያስተላለፈውን ውሳኔ ሽሮ ሕዝብ ከመረጠው ኮሚቴ ጋር ድርድር? ለምን? የሰይጣን ጆሮ አይስማው ነበር የሚባለው። አሁንማ ከመሰማቱም አልፎ ትዝብትን አሳድሯል።

ወሳኝ የሆነው ሁለተኛው ህዝባዊ ስብሰባ ለመካሄድ ትንሽ ቀናት ሲቀረው ከሽግግር ኮሚቴው ጋር ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ከመጀመሪያውም ሲጠነሰስ ኮሚኒቲውን የፖለቲካ መጠቀሚያ በሚሆን መልኩ ለማዋቀር እቅዳቸው አልሳካ ሲላቸው በድሮው ኮሚኒቲ እንዲጠቀሙ ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩት ሦስት ግለሰቦች ስማቸውን በበተኑት ወረቀት ላይ አስፍረው ወደ ፅሁፋቸው መደምደሚያ ላይ የሚከተለውን አቋማቸውን ገለፁ። “የሕዝቡን አንድነት የማህበረሰቡን ሰላም የኮሚኒቲውን ነፃነት እየተከላከልን መሆኑን በማመን፤ ስብሰባውም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ስላይደለ፤ የበታኝና ከፋፋይ ቡድን ስብሰባ ስለሆነ በ 12/18/11 ለሚደረገው ስብሰባ ላለመገኘት ተገደናል። በተረፈ አንድነታችን በሚጠበቅበት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በሻርለት በሚጠራው ስብሰባ ለመገናኘት ቸር ይግጠመን።” እንግዲህ ለአባይ ግድብ እናዋጣ፣ ብንዲራው ትክክል አይደለም፣ በ Oct. 15, 2011 በተካሄደው ስብሰባ ሳይቀር የአባይን ግድብ የምትል ተከተለኝ በዚያው ኮሚኒቲ እናቋቁማለን አስከማለት ከመድረስም በየመካከሉ የቻሉትን ሁሉ ቢያደርጉም ኮሚኒቲውን በሚፈልጉት መንገድ ማዋቀር ስላልቻሉ ነገር ግን በድሮው ኮሚኒቲ እንቀሳቀሳለን በማለት የድሮውን ኮሚኒቲ ሊቀመንበር ይዘው ለመንቀሳቀስ በመወሰናቸው ነው ይህን የመጨረሻ ወረቀት የበተኑት። እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ወጣ ውረድ በኋላ ስይሳካላቸው ስለቀረ ለጌቶቻቸውና ለራሳቸው የተሰጣቸውን ስም መልሶ ለሕዝብ ተመራጮች በመስጠት ሊለዩ የወሰኑት። ይህም አካሄድ ያው የጌቶቻቸው አካሄድ ነው። እነሱ ከየት ያመጡታል ብላችሁ ነው? ህዝቡ በቃ! ሲል እነመለሰ እንደገና በቃ! አሉ ነው የተባለው ባንድ ወቅት? ያም ሆነ ይህ ሕዝቡ Dec. 18, 2011 ተሰብስቦ የራሱን መሪዎች

በማስመረጥ በቃለ መሓላ እንዲመሩን በጥሩ ስነስርዓት ሲደመድም የወያኔ ተላላኪዎችም ተልዕኮ በሻርለት ገና ከመጀመሪያው ሞቶ ተቀብሮባቸዋል እርማቸውን ያውጡ። በድሮው ኮሚኒቲ ስም እንቀጥላለን እንኳን ቢሉ የወያኔና የዘር ሰለባ የሆነ ኮሚኒቲ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

በመጨረሻም አንድ ከዚህ ከኮሚኒቲ ጋር የተዛመደ የወያኔ አካሄድን በማስታወስ ነገሬን ልቋጭ። ወያኔ በውጭ ሀገር በድብቅ ሲያራምደው የነበረውን በይፋ ለማካሄድ እንዲያመቸው "የዲያስፖራ ረቂቅ ፖሊሲ" ለውይይት የቀረበ መነሻ ሀሳብ በሚል እያሰራጨ ያለውን ባለ 24 ገፅ ዶሴ ማንበቡ ይህ በኮሚኒቲ እና በሃይማኖት ውስጥ ለመግባትና አኩይ አላማውንም ለማስፈፀም የሚደረግ ጥረት ሁሉ የዚሁ አካል መሆኑ ግልፅ መሆን አለበት እላለሁ። ይህን ለውይይት የቀረበ የዲያስፖራ ረቂቅ ፖሊሲ የሚሉትን ማስፈፀም የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው የሚገኙትበትን ተቋም ሁሉ በግልፅም ሆነ በስውር በሚንቀሳቀሱ ወያኔዎች እንዲሁም ለሆዳቸው ባደሩ ምንደኞች ካሲያዙ በኋላ ስለሚሆን ከወዲሁ ልናውቀው እና ነቅተን ልንጠብቀው ይገባል።

አንድነት በላይ

yagerlig@gmail.com